# የማህበረሰብ ውይይት /Community Conversation/ ለበለጠ ውጤት

ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሀገራችን ከተከሰተ ጊዜ አንስቶ ቫይረሱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይቷል። በክልላችንም ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ መዋቅሮች የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤቶች ስራ አመራር ቦርዶችና ሴክሬታሪያቶች እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ የቀበሌ ኤድስ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመሩ ከሁለት አመት በላይ ሆኗል። ባሉፉት አመታት ህ/ሰቡን ያሳተፉ ዘላቂ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎችን ለማከናወን በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ለፕሮግራሞች ተፈጻሚነት ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች የተገኙ የገንዘብና የቁሳቁስ ዕርዳታዎች ለየወረዳዎች እንዲደርስ ተደርጓል። ከእነዚህም ውስጥ በ49 የክልሉ ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኙ ቀበሌዎች ከማዕከል ቀጥታ በተላከላቸው የገንዘብ ድጋፍ ራሳቸው በቀረጿቸው ዕቅዶች በራሳቸው ፈጻሚነት የቅስቀሳና ትምህርት፣ ድጋፍና እንክብካቤን፣ የኮንደም ስርጭት፣ የሁለንተናዊ ጥንቃቄ እና የመሳሰሉ ተግባራትን እንዲፈፅሙ የተደረገው ይገኝበታል። በዚህ መሠረትም በ49 ወረዳዎች ከ5.6 ሚሊየን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ «የወረዳ ግራንት» በሚባለው ፕሮግራም አማካኝነት ለቀበሌዎች ተልኮ ስራዎችን በጥቂት ወጪና በህ/ሰቡ ሁለተናዊ አስተዋጽኦ መስራት መቻላቸውን በተግባር አስመስክረዋል።

ከዚህ ተሞክሮ በመነሳትም የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት ለሌሎች ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ይህንን የወረዳ ግራንት አካሄድ/ስልት/ እንዲከተሉ ግፊት እያደረገ ነው። የዚህ መነሻ ደግሞ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ምላሽ ፍጹም ማ/ሰቡን አቅም የሚያጐለብት፣ አካባቢያዊ ክህሎትን፣ አቅሞችን፣ እውቀቶችን እሴቶችን ወ.ዘ.ተ በሚገባ የሚጠቀም በተጨማሪም ይህንን ከፍተኛ የማህበረሰብ አካባቢያዊ አቅም የማያመክን፣ የህ/ሰቡን ተነሳሽነት የሚያቀጭጭ፣ አዋጭና ዘላቂነት ያለው መሆኑ የግድ ስለሚያስፈልግ ነው። ምንም እንኳን በወረዳ ግራንት ፕሮግራም በሌሎች አካላት አማካኝነት የተከናወኑት አብዛኛዎቹ ስራዎች ውጤት የታየባቸው መሆኑ ባይካድም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሚጠይቀወ ስር ነቀል ለውጥ፣ ሽፋንና ውጤት አንጻር እጅግ አነስተኛ ነበሩ። ከስራቸው ጥራት ስርጭትና የማህበረሰብ ተሳትፎ አንጻር ስናያቸውም በርካታ ክፍተቶች ይታዩባቸዋል። ዘላቂና አዋጭ ያልሆኑና የህሰቡን አቅም በሚገባ ያልገነቡም ነበሩ።

በአሁኑ ሰዓት በክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተያዘው አቅጣጫ ደግሞ የትኛው የኤች አይ ቪ/ኤድሰ ምላሽ የህ/ሰቡ ንቅናቄና ተሳተፎ የሚያርጋግጥና ህ/ሰቡ የራሱን ችግር እራሱ የማፈታበትን አቅም የሚገነባ ዘላቂ የሆነ ጠባቂነትን የማይፈጥር ወጪ ቆጣቢና ሰፊ ሽፋን ያለው እንዲሆን ማድረግ ነው። በተጨማሪም እንቅስቃሴው አካባቢያዊ እሴቶችን እውቀቶችን ጠቃሚ ልምዶችን እና መሰል አቅሞችን አሟጦ የሚጠቀም፣ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚነሳና በችግሩ መሠረታዊ ምንጭ ላይ ያተኮረ፣ ወጥ፣ የተቀናጀ፣ የተገኙ መልካም አጋጣሚዎች ሁሉ የሚጠቀምና ተቋማዊ መሠረቶችን የሚጥል/የሚያጠናክር/ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ሊሆን ይገባል። በተለይ በማህበረሰብ ደረጃ የህዝብ ንቅናቄን የመፍጠሩ አስፈላጊነት በሚገባ ስለታመነበት በግንቦት 1996 ዓ.ም የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ የክልላዊ የፀረ-ኤድስን የሕዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ አጽድቋል። የዚህ ሰነድ ዋነኛ አላማና ግብ ደግሞ ከላይ ያነሳናቸውን አይነት ማህበረሰባዊ ምላሾች እውን በማድረግ ለኤድስ የማይመች ሕብረተሰብ(AIDS competent society) መፍጠር ነው። ሰነዱ ለዚህ አላማ እንደ ቁልፍ የማስፈፀሚያ መሳሪያ ካስቀመጣቸው ስልቶች ግንባር ቀደሙ የማህበረሰብ አቅም በማህበረሰብ ውይይት የማበልፀግ (CCE-CC) ሒደት ነው። ይሕ ስልት በትንሽ ወጪ በርካታ ውጤቶችን በማህበረሰቡን ደረጃ ለማምጣትና ከሁሉም በላይ የማ/ሰቡን ሁለንተናዊ አቅም ለማጐልበት የህ/ሰቡን በራሱ ጉዳይ በንቃት የመሳተፍ፣ ራሱን የመገምገም፣ ችግሮችን የመለየት፣ የማቀድ፣ ወዘተ ክህሎትና ስርአት የሚፈጥር ወሳኝ ስነ-ዘዴ ነው። በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት በክልላችን ይህንን ስነዘዴ በየቀበሌው ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። ከእነዚህ ጥረቶች አንዱ የወረዳ ግራንት ፈንድ ተጠቃሚ ቀበሌዎች ከግራንት ፈንድ በሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ በዋናነት ከሚሠሯቸው ስራዎች ቀዳሚው የማህበረሰብ ውይይት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ነው። ይሕ የማህበረሰብ ውይይት ከወረዳ ግራንት ፈንድ ተግባራት አንዱ እንዲሆን በክልላችን ብቻ ሳይሆን በብሔራዊ ደረጃም እንደአቅጣጫ ተቀምጧል።

በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት የችግሩ ባለቤት በሆነው ህ/ሰብ ንቁ ተሳትፎ መሠራት ያለባቸው ናቸው፡፡ ሌሎች በተቋምና በፖሊሲ ደረጃ የሚከናወኑ ደጋፊና አገልግሎት ነክ የሆኑ ስራዎችም አሉ፡፡ እነዚህ በተቋምና በፖሊሲ

ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት የማህበረሰቡን አቅም ለማጐልበት፣ አዳዲስ የአሠራር ስልቶችንና ተሞክሮዎችን ለማስረጸት፣ ለሕ/ሰብ ተገቢውን አገልግሎት በጥራትና በስፋት ለማድረስ፣ ህ/ሰቡ ለሚያከናውናቸው ዘርፈ ብዙ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ወዘተ የሚረዱ ናቸው፡፡ ከመከላከል፣ ድጋፍና እንክብካቤ፣ ተጋላጭነትን ከመቀነስ ወዘተ የተያያዙ ዋና ዋና ተግባራት ግን በማህበረሰቡ በራሱ ተሳትፎ የሚከናወኑ መሆን አለባቸው፡፡

የማህበረሰብ አቀፍ ስራዎችን እውን ማድረግ የምንችልባቸው መሠረታዊ የአስተዳደር ዕርከኖች ደግሞ ቀበሌዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀበሌ ደረጃ ለሚሠሩ ስራዎች ትኩረት መስጠትና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማበረታታት ወሳኝ ይሆናል፡፡ በቀበሌ ደረጃ ማ/ሰቡ ሊያከናውናቸው የሚገቡ እንደ ማህበረሰቡ ፍላጐት፣ አቅም፣ ወዘተ የሚወሰኑ በመሆናቸው እያንዳንዱ ወረዳ/ቀበሌ ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ጋር የተያያዙ በርካታ ተግባራት መኖራቸው እውነት ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ በአይነት፣ በአፈጻጸም በመጠንና መሰል ሁኔታዎች እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ በመነሳት የሚወሰናቸው ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ግን ይሕንን የማህበረሰብ በፍላጐቱና ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረቱ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች የማቀድ፣ የመተግበር መብት በማይጻረር መልኩ እንደ ሁኔታው ማሻሻያ እያደረገ ሊተገበራቸው የሚገቡ ዋና ዋና የእንቅስቃሴ አቅጫጣዎችን መጠቆሙ ተገቢ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በቀበሌ ደረጃ እንዲተገበሩ የሚጠበቁ ቁልፍ ተግባራት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ይሆናሉ፡፡

1. **መረጃ፣ ትምህርትና ቅስቀሳ/የባህሪ ለውጥ ኮሚይኒኬሽን /IEC/BCC/**

በዚህ ስር በርካታ ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ በቀበሌ ደረጃ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎት/ቡድኖች/ ውስጥ የማህበረሰብ ውይይት ማካሄድ፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን የኤች አይ ቪ/ኤድስና ተያያዥ ሁኔታዎችን መረጃ ማሠባሰብ፣ ማጠናቀርና ማሠራጨት፡፡ ለዚህም የሚረዳ የቀበሌ የኤድስ መረጃ ስርአት መዘርጋትና የመረጃ ማዕከል መመስረት፡፡ እንዲሁም በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ለቀበሌው ሕ/ሰብ ትምህርት የሚሠጡ፣ መረጃ የሚያስተላልፉ፣ የሚቀሰቅሱ ልዩ ልዩ የሕትመት፣ የኦዲዮ እና መሠል ውጤቶችን ከተለያዩ አካላት /አካባቢዎች/ በማሰባሰብ ለሕብረተሰቡ የማዳረስ ተግባር በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

2. **ኮንደምን ማስተዋወቅና ማሰራጨት**

ኮንደም ከሶስቱ ዋና ዋና የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ መንገዶች አንዱ ነው፡፡ በሌላ መልኩ በኮንዶም ዙሪያ የተለያዩ ማህበረሰቦች የእምነት ተቋማት የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው፡፡ ከእምነትና ከሌሎች ሁኔታዎች በመነጨ ምክንያቶች የሚደግፉና የሚቃወሙ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን ህ/ሰቡ የኮንደም አማራጭ መኖሩን ሊረዳ ይገባል፡፡ ህብረተሰቡ እውነቱን ከተረዳ በኋላ የሚመቸውን/ያመነበትን/ አማራጭ የመጠቀም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ማንኛችንም በየትኛውም ግለሰብ የህልውና ጥያቄ ላይ ልንወስን አንችልም፡፡ ምርጫው የግለሰቡ ነው፡፡ የሀይማኖት ተቋማት በጉዳዩ ዙሪያ እምነት ከሌላቸው ኮንደምን እንዲያስተዋውቁ አይገደዱም፡፡ ነገር ግን ሌሎች እንዲያስተዋውቁም ሆነ እንዳይጠቀሙ ሊያስገድዱ ወይም ሊቃወሙ አይችሉም፡፡ በዚህ ዕውነት ላይ በመመስረት በቀበሌ ደረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ኮንዶምን የማስተዋወቅና የማሠራጨት ስራ ይካሄዳል፡፡

3. **ድጋፍ፣ እንክብካቤና ህክምና**

በቀበሌው የሚገኙ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህጻናት እና ቤተሰቦቻቸው በሕብረተሰቡ ተሳትፎ ድጋፍ እንክብካቤ የሚያገኙበት ቀጣይነት ያለው ስራ ይሰራል፡፡

4. **በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምክርና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራና /ሌሎች አገልግሎቶች፡-**

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከሉ ረገድ በክልላችን ከታዩት በጐ ጅምር ስራዎች መካከል በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎቶች ማዕከላት መስፋፋትና በእነዚህ ማዕከላት የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡

ይሕንን በጎ ጅምር በገጠርና በከተማ ደርጃ አጠናክሮ መቀጠል ይቻል ዘንድ በቀበሌ ደረጃ ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎትን ማስተዋወቅና ማስፋፋት ይሆናል፡፡

## 5. <u>ሰብአዊ መብቶች /Human Rights/</u>

የእምነት ተቋማት አገልግሎት ሰጪዎች፣ የስራ ቦታዎች፣ ግለሰቦች ወ. ዘ. ተ ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወገኖችን የህፃናትንና የሴቶችን ሰብአዊ መብት እንዲያስከብሩና እንዲያከብሩ ማስተማር ማበረታታት መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይ ከውርስ ከንብረትና ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ አብሮ የሚደርሱ ኢፍትህዊ ክስተቶች ተገቢ ፍትሕ እንዲያገኙ ከትትል መደረግ አለበት፡፡ እንዲሁም ሴቶች በአስገድዶ መድፈር በጠለፋ በባህላዊ የጋብቻ ሁኔታዎች፣ በሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አልያም ሆነ ተብለው በሚፈፀሙ ጥቃቶች የተነሳ ለኤች አይ ቪ እንዳይጋለጡ የህግ ከለላ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡ ህ/ሰቡ ይሕንን አይነት ሕገ-ወጥ ተግባር እንዲታገልና እንዲያወግዝ ማበረታታት እና ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚመለከታቸው አካላት ይህንን ተገንዝበው የነቃ ተሳተፎ እንዲያደርጉ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

## 6. ተጋላጭነትን መቀነስ/ Vulnerability Reduction/

ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ለአስከፊው ኤች አይ ቪ/ኤድስ በእኩል ደረጃ የተጋለጡ አይደሉም፡፡ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖማያዊ ተፅኖዎች ሳቢያ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለቫይርሱ ተጋላጭ የሆኑበት ሁኔታ በማህበረሰብ ውስጥ በስፋት ይታያል፡፡ በመሆኑም ይሕንን ችግር ለመቀነስ በማህበረሰብ ውይይት አማካኝነት ውጤታማ ስራ ሊሠራ ይገባል፡፡ በቀበሌው ለሚገኙ ስራ አጥ ለሆኑ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ በወሲብ ንግድ ለተሰማሩና የጎዳና ተዳዳሪ ለሆኑ ወገኖች ህብርተሰቡ፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር እንዲደራጁና በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሰራዎች እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሰራ ይሰራል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ተግባራትን በቀበሌ ደረጃ በማህበረሰቡ ውይይት አማካኝነት ማከናወን ቫይረሱን ለመከላከል የሚደርገውን እንቅስቃሴ በብዙ መልኩ እንደሚያጠናከረው ይታመናል፡፡ ይህን ታላቅ የሆነ ሕብረተሰቡን የማንቃትና የማደራጀት ስራ ውጤታማ ለማድረግ ሁሉም የበኩልን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡ በእስካሁኑ እንቅስቃሴያችን ቫይረሱን በመከካከሉ ረገድ ሁሉም ኃላፊነቱን በብቃት እንዳልተወጣ በተደጋጋሚ ሲገለፅ ቆይቷል፡፡ በቀጣይ የሚኖረን ጉዞ ይህ ሁኔታ መቀጠል የለበትም፡፡ ይሕ ሁኔታ ከቀጠለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሕብረተሰቡ ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋት በብዙ መልኩ እያደገ ሊሄድ እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡

ይሕ እንዳይከሰት ደግሞ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በቀጣይ በክልላችን ተጠናክሮ ሊካሄድ በተጀመረው የማሕበረሰብ ውይይት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ለመሆኑ ይሕን የማሕበረሰብ ውይይት የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ይቻል ዘንድ ከተለያዩ የሕብርተሰብ ክፍሎች ምን ይጠበቃል? ቀጥለን የወሰኑ የማሕበረሰብ ክፍሎች አብይ ድርሻ ምን እንደሚመስል በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## 1. የቀበሌ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ኮሚቴ

ይሕ አካል በቀበሌው ከሚገኙ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችና ተቋማት ከቀበሌ መስተዳድር፣ ከት/ቤቶች፣ ከሀይማኖት ተቋማት፣ ከፀረ-ኤድስ ክበባት ከእድሮችና ከታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ የተወከሉ ሰዎችን ያካተተ ነው፡፡ ኮሚቴው በቀበሌ ደረጃ የሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ ኤች አይ ቪ /ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን የማስተባበር ሀላፊነት በአዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

በዚህም መሠረት ይህ አካል ከቀበሌው አመራርና ከሌሎች ፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን በቀበሌው ውጤታማ የህዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ አካላት ወጥ በሆነ በተቀናጀና የማህበረሰቡን ተቀዳሚ ፍላጎት ባገናዘበና ሀብትን በግልፅነት፣ከብክነት በጸዳ መልኩ ጥቅም ላይ በማዋል ውጤታማ ሰራ እንዲሰራ ይንቀሳቀሳል፡፡

## 2. የቀበሌ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የጤና አገልግሎት ተቋማት

በአሁኑ ሰዓት በዋናነት በሽታን አስቀድሞ በመከላከል ሰራ ላይ ያተኮረ የማህበረሰብ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች በቀበሌ ደረጃ ለማሰማራት በክልሉ መንግስት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ሁሉም ቀበሌ ቢያንስ አንድ የጤና ኬላ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ እነዚህ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች በቀበሌ ደረጃ ለሚካሄደው የኤች.አይ.ቪ/ኤድሰ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት እጅግ ጠቃሚ ሀይሎች ናቸው በመሆኑም የጤና ኤክሰቴንሽን ባለሞያዎች በኤች አይ ቪ/ኤድሰ ዙሪያ በማህበረሰብ ውይይት አመቻችነት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች በቀበሌው ፀረ-ኤች አይ ቪ/ኤድሰ ኮሚቴ ውሰጥ በመሳተፍ የቴከኒክና የምክር አገልግሎት በመስጠት በቀበሌው እቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ወ.ዘ.ተ ይሳተፋሉ፡፡

## 3. የገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማትና የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች

ኤች አይ ቪ/አድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሰፊ ድርሻ ይኖራቸዋል ተብለው ከታመነባቸው አካላት መካከለል በየወረዳው የሚቋቋሙ የገበሬ ማሰልጠኛዎች ናቸው፡፡ ልሉ ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ በእነዚህ ማእከላት ገበሬው ስልጠና የሚሠጡ ከሶሰት ሺ በላይ አሰልጣኞችን በማሰልጠን ላይ ሲሆን እነዚህ አሰልጣኞች በኤች አይ ቪ/ኤድሰና ማህበርሰብ ወይይት ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ማዕከላቱ ስራቸውን ሲጀምሩ ከየቀበሌው የሚወጣጡ ገበሬዎች በማዕከላቱ ለወራት የሚቆይ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ቆይታ ወቅት ገበሬዎች ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ያተኮረ ትምህርት በየሳምንቱ ለተወሰኑ ሰዓታት እንዲሰጣቸው ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከገበሬው ጋር በሚኖራቸው የጠበቀ ግንኙነት ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያግዙ በርካታ ተግባራትን ይፈፅማሉ፡፡

## 4. ት/ቤቶችና ሌሎች የትምህርትና ስልጠና ተቋማት

እነዚህ ተቋማት የወጣቶችንም ሆነ የአጠቃላይ ማህበረሰቡን አመለካከት አኗኗር የእርስ በእርስ ግንኙት በመቅረጽ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ይህንን የት/ቤቶች ታላቅ ሚና በመገንዘብ በየት/ቤቶች የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ «የትምህርት ቤቶች ግራንት ፈንድ» ፕሮግራም ቀይሶ በክልሉ በሚገኙ 200 ት/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ በነዚህ ተቋማት የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ መንገድ ያገኙትን እውቀት ስራ ላይ እንዲያወሉት ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም እነዚህ አካላት የቀበለው ፀረ-ኤድስ ኮሚቴና ሌሎች ፈጻሚ አካላት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ በንቃት በመሳተፍ የሚጠበቅባቸውን የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የቁሳቁስና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ ሀላፊነታቸው ሊወጡ ይገባል፡፡

## 5. የሐይማኖትና ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት

የሀይማኖትና ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት መሪዎች እና ሌሎች ተስሚነት ያላቸው አካላት የማህበረሰቡን ስሜት በመግዛት ወደ አንድ አቅጣጫ ለመምራት ተወዳዳሪ የላቸውም፡፡ በመሆኑም እነዚህን ወሳኝ አካላት በአግባቡ ከተጠቀምን አብዛኛውን ህብረተሰብ መድረስ ይቻለናል፡፡ የምናካሂደው ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ ስኬታማነት በእነዚህ ሀይሎች ሊሳካ አሊያም ሊኮላሽ ይችላል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ዕንቅስቃሴ እነዚህን አካላት በንቃት ያሳተፈና በእነርሱ ግንባር ቀደምትነት የሚመራ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለዚህም ነው በቀበሌ ፀረ-ኤች አይ ቪ/ኤድስ ኮሚቴ ውስጥ እነዚህን አካላት አባል እንዲሆኑ የተደረገው፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው በሚደረጉ የማህበረሰብ ውይይቶች ላይ የነቃ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከማህበረሰብ ውይይቶች በሚገኙ የመፍትሔ ሀሳቦች መነሻነት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለአባሎቻቸው ትምህርት በማስተላለፍ ሀላፊነታቸውን መወጣት ይጠ በቅባቸዋል፡፡

«ኤድስን በጋራ እንከላከል»

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት
የኢንፎርሜሽን ቡድን
ስ.ቁ 20 54 06